በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን!!!

የደብረ ብርሃን ቅዱስ አማኑኤል ወበአታ ለማርያም ቤተክርስቲያን በሁለት ሺህ ሰባት  ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ብዙ ፈታናውችንና ውጣ ውረዶችን አሳልፏል

ቤተክርስቲያናችን በ፲፱፺፱ ዓ.ም (2007) በብፁዕ አቡነ ማርቆስ በወቅቱ በሰሜን አሜሪካ የምዕራብ ሃገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ተባርኮ መጠሪያ ስሙ ደብረ ብርሃን ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ተብሎ ተከፈተ።

ቤተክርስቲያን በሚከፈትበት ወቅትም መልአከ ኪዳን ቀሲስ ሳሙኤል የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን በላስቬጋስ አስተዳዳሪ አስፈላጊውን ንዋየ ቅድሳት በማበርከትና ዲያቆናትንና መዘምራንን ይዘው መኪና ነድተው በመምጣት ለደብረን ምሥረታ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገዋል።

ከ፲፱፻፺፱- ፳፻ (2007-2008) ብፁዕ አቡነ ማርቆስ በተደጋጋሚ እየተመላለሱ ሲያገለግሉንና ሲያበረታቱን የቆዩ ሲሆን በተጨማሪ  መልአከ ኪዳን ቀሲስ ሳሙኤል ደጀኔ በወቅቱ የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ወቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በላስ ቬጋስ አስተዳዳሪ በቴሌ ኮንፍረን በየሳምንቱ እሁድ እሁድ ቃለ ወንጌል ሲያስተምሩንና ሲያበረታቱን ቆይተዋል።

ከ፳፻-፳፻፪ (2008-2010) ድረስ ብጹእ አቡነ ማርቆስ ዲሲ አካቤቢ ያገኟቸውን ካህን እኔ አላውቃቸውም ግን እስኪ እይዋቸው ብለው  በመልአከ መዊዕ አባ ገብረኪዳን አምሐ ልከውልን አገልግሎት ሲሰጡ ቢቆዩም እኚህ አባት በሃይማኖት ሕጸጽ ችግርና በሥነ ምግባር ጉድለት የአባላቱን ትዳር እስከማፍረስ የደረሰ እንኳን ከመነኩሴ ካህን ከአንድ ክርስቲያን በማይጠበቅ መልኩ የጥፋት ሰው ሆነው ስለተገኙና በጥንቆላ መንፈስ ስለታዩ ደብሩን ለቀው እንዲሄዱ ተደርጓል።

ከ፳፻፪-፳፻፫ (2010-2011) በወቅቱ ከአባ ገብረኪዳን ጋር በዲቁና ሲያገለግሉ በነበሩት በመምህር ዓይነኩሉ ቃለ ወንጌልን ስንማር የቆየን ሲሆን አልፎ አልፎ ካህን በማስመጣት የቅዳሴ አገልግሎት ሲከናወን ቆይቷል።

ከ፳፻፫-፳፻፲፪ (20011- 2020) መምህር ዓይነኩሉ ትዳር መሥርተው ቅስና ከተቀበሉ በኋላም በዩታ መቆየት የባለቤታቸው ፈቃድ ስላልሆነ ቦታውን ለቀው ከሄዱ በኋላ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ካህናት እየተጋበዙ ሲያገለግሉን ቆይተዋል

ይህ በእንዲህ እንዳለ መደበኛ አገልግሎት ፍለጋ ከነቤተሰቦቻቸው ከ27 የሚበልጡ ምዕመናን ስቴቱን ለቀው ቤተክርስቲያን ወዳለበት ቦታ ተሰደው በመሄድ ለራሳቸውና ለልጆቻቸው በመንፈሳዊ ሕይወት ለመጠቀም የቻሉ ሲሆን ከመካከላቸውም ልጆቻቸውን ዲያቆን እና ዘማሪ ለማድረግ የቻሉ አሉ። በአንጻሩ እዚህ የቀረነው አባላትና ልጆቻችን ከሃይምኖት ርቀን ቀርተናል: በተለይ ልጆቻችን ፈጻመው ከሃይማኖት እንዲርቁ ሆንዋል ።

 ይሁን እንጂ በዚህ የቆዩት ከመሥራች አባላቶች መካከል ግርማይ ታደሰ ፣ተክሉ አደነ ፣ቢሻው ፈለቀ እና ሱራፌል በትሩ በጋራ በመሆን የቤተክርሲያኑን ፈቃድ በየዓመቱ በማሳደስ አልፎ አልፎም ካህናትን በመጋበዝ ምእምናን በማሰባሰብ ቅዳሴ በማስቀድስ ቤተክርስቲያኑ እንዳይዘጋ በማደረግ ለረጅም ጊዜ የአቅማቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ ቆይተዋል።

በተጨማርም ግርማይ ታደሰ ለ12 ዓመታት አንድ ክፍል ቤት በማዘጋጀት ንዋየ ቅድሳትን በጥንቃቄ በማስቀመጥ እስከ 2019 ዓ.ም ድረስ በማቆየት መልአከ ብሥራት ቀሲስ ገብረ እግዚአብሔር ሲመጡ ለእርሳቸው አስረክቧል።

በ፳፻፱ (2017) ሁሉት ሲኖዶስ የነበረው  አንድ ሲኖዶስ ሲሆን የደብሩ ሰበካ ጉባኤ ምክትል ሊቀመንበር የሆነውን የግርማይን ልጅ ክርስትና ለማንሳት የመጡት መልአከ ኪዳን ቀሲስ ሳሙኤል የደብረ ብርሃን ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያንና በአሜሪካ ሲኖዶስ ሥር የነበረው የማርያም (ኪዳነ ምህረት) ቤተክርስቲያን የሁለቱም ምዕመናን ቁጥራቸው አነስተኛ ስለሆ ሁለት ቤተክርስቲያን ከመሆን ይልቅ አንድ ቤተክርስቲያን ሆነው  በአንድነት እንዲያገለግሉ አበክረው በማሳሰብ ሁለቱን አቢያተ ክርስቲያናት የሚለያያ የሁለት ሲኖዶስ ግንብ አንድ በመሆን ስለፈረሰ አንድ ሁኑ በማለት በኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን ተገኝተው አስተምረው መክረው የሄዱ ሲሆን ለተወሰነ ጊዜ ወደ ኪዳነ ምሕረት (ማርያም) እየሄድን መገልገል የጀመርን ቢሆንም በአስተዳደር ላይ ያሉት የኪዳነ ምሕረት አባላትና ካህኑ መልአከ ጽዮን አባ ፍሥሐ እጃቸውን ዘርግተው በመቀበል

ፊንታ ፊት በመንሳት በማግለል ደስተኛ አለመሆናቸውን ስላሳዩን ምንም እንኳን ቤተክርስቲያን የበሥላሴ ስም የተጠመቁ የክርስቲያኖች ሁሉ ቤት ብትሆንም በቤተችን ባይታወርነት እንዲሰማን ስላደረጉና በተጨማሪም ልጆቻችንን ዲቁና አስተምሩልን ብለን  ለመልአከ ጽዮን ኣባ ፍሥሐ ብንሰጥ እንኳንስ ግብረ ዲቁና ሊያስተምሩ ይጾሙ የነበሩትን ልጆች አትጹሙ በማለት እንዳይጾም በማድረግ ማከላከል ስለጀመሩና ፣ ከቤተክርስቲያን ሥርዓት ውጪ በሆነ ንግግር "ድሮ በልተን ነበር የምንቀድሰው ዛሬ ለውጠውብን ነው እንጂ" ወዘተ የሚል የተሳሳተ ስብከት መስበክ ስለጀመሩ አብሮ ለማገልገልና ለመገልገል ሳይቻል ቀርቷል።

በመጨረሻም ከ፳፻፲፪-፳፻፲፯ (2020-2024) መልአከ ብሥራት ቀሲስ ገብረ እግዚአብሔር ለሁለት ዓመት በየሳምንቱ ቄስም ዲያቆንም በመሆን ሲያገለግሉን የቆዩ ቢሆንም በማርያም (ኪዳነ ምህረት) ቤተክርስቲያን በኩል ያሉ የቦርድ አባላትና መልአከ ጽዮን አባ ፍሥሐ ለአካባቢው ምዕመናን ታቦት የላቸውም፣ መናፍቃን ናቸው ወዘተ የሚል አሉባልታ በመንዛትና መልአከ ብሥራት በሁለቱም አቢያተክርስቲያናት አገልግሎት እየሰጡ ከስድስት ወር በላይ ለአንድነት ብዙ ጥረት ቢያደርጉም ከማርያም ቤተክርስቲያን እንዳይደርሱ በማገድና ለፖሊስ ሪፓርት እናደርጋለን የሚል ማስፈራሪያ በቴክስት በመላክ ስለከለከልዋቸው ሁለቱን አቢያተ ክርስቲያናት አንድ የማድረግ ጥረቱ ሳይሳካ የቀረ ከመሆኑም በላይ በኪዳነ ምህረት የቦርድ አባላትና ካህን በሚነዛው የሐሰት ወሬ የተነሣ የደብሩን ምዕመና በአንድነት ለማስተባበርና በሚገባ ማሰባሰብና ማጠናከር ስላልተቻለ  ወደ ፊኒክስ አሪዞና ሙቭ ያደረጉ ሲሆን ነገር ግን ቢያንስ በየወሩ እየመጡ በመቀደስ አገልግሎታችን እንዲቀጥል ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። በተጨማሪም በዚህ የወርሃዊ አገልግሎት መልአከ ኪዳን ቀሲስ ሳሙኤል ደጀኔ እየመጡ ሲያገለግሉን ሲያበረታቱን ቆይተዋል።

በ፳፻፲፯ (2024) ከኢትዮጵያ መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ ሰሎሞን ቶልቻ በመልአከ ብሥራት ቀሲስ ገብረ እግዚአብሔር አማካኝነት በቋሚነት ሊያገለግሉን ከጥቅምት ፩ ፳፻፲፯ (October 11, 2024) መጥተው የነበረ ቢሆንም ቤተክርስቲያኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ የኢሚግሬሽን ፕሮሰሳቸውን ለማስፈጸም የማይችል በመሆኑ ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ተገደዋል።

እኛም ለምልሞ የነበረው ተስፋችን ፈጥኖ ቢጨልምም አይዟችሁ እኔ አለሁ አስፈላጊ ከሆነም ሙቭ አድርጌ አገለግላችኋለሁ ብለው በማጽናናት መልአከ ኪዳን ቀሲስ ሳሙኤል ደጀኔ በወር የነበረውን አገልግሎት በየሳምንቱ በማድረግ ከላስቬጋስ በየሳምንቱ በመመላለስ ሲያገለግሉን ቆይተዋል።

ከየካቲ ፲፮ ፳፲፯ ጀምሮ ደግሞ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሞቀና የተመቻቸ ቤታቸውንና ኑሮአቸውን ትተው ራሳቸውን ለተጨማሪ ወጪ ዳርገው የተገፋነውንና በጥሩ አገሊጋይ እጦት አስራ ስምንት ዓመት ሙሉ ማደግና መሻሻል ያልቻልነውን ልጆቻቸውን ለማገልገልና ለማጠናከር በመንፈሳዊ ቅናት ተነሣስተው  ወደ ዩታ ሙቭ በማድረግ ሙሉ አገልግሎት እየሰጡን ይገኛሉ።

በጨማሪ መልአከ ኪዳን ቀሲስ ሳሙኤል ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት ወደ ሕብረት ለማምጣት አንድ ለመሆን ባይቻል እንኳን በክብረ በዓላት የጋራ አገልግሎት ለማድረግ እንዲቻል  በቃልም በጽሑፍም በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ከኪዳነ ምህረት(ማርያም) ቤተክርስቲያን የቦርድ አባላት በኩል መልስ ሳያገኙ ቀርተዋል። ሃገረ ስብከቱም ይህንኑ ሐሳብ ተቀብሎ ቀን ወስኖ ሁለቱ ካህናት ማለትን መልአከ ጽዮን አባ ፍሥሐና መልአከ ኪዳን ቀሲስ ሳሙኤል  አንዳቸው አንዳቸው ቤተክርስቲያን  በመሄድና በማገልገል የማቀራረብ ሥራ እንዲሠሩ በጽሑፍ ከሃገረ ስብከቱ መመሪያ ቢሰጥም በኪዳነ ምህረት(በማርያም) ቤተክርስቲያን ኃላፊዎች በኩል ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል።

በሌላ በኩል መልአከ ብሥራት ቀሲስ ገብረ እግዚአብሔር እና አቶ ግርማይ ታደሰ  በጋራ በመሆን ከኢትዮጵያ ወደ ዩታ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ  መምጣታቸውን ሰምተው ስልካቸውን አፈላልገው በመደወልና ተቀብለው በማስተናገድ ከተዋወቅዋቸው በኋላ ከሞርማን ቸርች (LDS) ጋር ያላቸውን የሥራ ግንኙነት ሲረዱ አጋጣሚውን በመጠቀም የመገልገያ ቦታ እንዲጠይቁላቸው በማድረግ  በሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ አማካኝነት ለ LDS church (ለኤል ዲ ኤስ ቸርች)  ቋሚ የመገልገያ ቦታ ለማግኘት  ያስቻለን ዘንድ በAugust 14/2021 በቁጥር 006 Edward (ኤድዋርድ) ለተባለ ተወካይ ደብዳቤ በመጻፍና በኢሜል በስልክ በመደዋወል ከብዙ ጥረት በኋላ በዓመቱ መገልገያ ቦታ መፈቀዱን ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ

ለመልአከ ብሥራት ቀሲስ ገብረ እግዚአብሔር ደውለው ያሳወቁ ሲሆን ይህን ደስታና የምሥራች የኪዳነ ምሕረት(ማርያም)ቤተክርስቲያን ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ማካፈል አለብን በማለት ለአንድነትና ለሰላም ይረዳል ብለን ጉዳዩን ገልጸንልናቸው ቦታውን አብረን እንድንረከብ ተስማምተን የሁለቱም አቢያተክርስቲያናት 501 (c) 3 ገብቶ ቦታውን ለመረከብ ከሁለቱ አቢያተ ክርስቲያናት አንድ አንድ ተወካዮች አቶ ስለሺ ታደሰና ግርማይ ታደሰ የተወከሉ ቢሆንም የኪዳነ ምህረት ወይን የማርያም የቦርድ አስተዳደር አባላትና መልአከ ጸዮን አባ ፍሥሐ አንድነቱን ባለመፈለግ በእኛ በኩል የተገኘውን ቦታ ለብቻቸው ለመረከብ ውስጥ ውስጡን ከብጹእ አቡነ ናትናኤልና ከሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ጋር ሆነው በመሥራት ብዙ ርቀት ሄደው እኛ እንድንገለል አድርገዋል።

በወቅቱም ይህን ጉዳይ ለሃገረ ስብከቱ በደብዳቤም፣ በቴክስትም ፣ ስልክ በመደወልም ብናሳውቅም መልስ የሚሰጠን ስላጣን ለLDS church እና sterling foundation ተወካዮች በማሳወቅ ሊሰጥ በተመረጠው ቦታ ላይ ያለውን የሪሞዴሊንግ ሥራ እንዲቆም ማድረግ የተቻለ ሲሆን በዚህ ወቅት ብጹዕ አቡነ ናትናኤል የኮላራዶና አካባቢው ሃገረ ስብከት ሊቀጳጳስ የደብረብርሃን ቅዱስ አማኑኤልን የሰበካ ጉባኤ አባላትን ሰብስበው በእኔ ይሁንባችሁ በቆቤ እምላለሁ ይህ ቦታ ሥራው እንዳለቀ ከሁለቱም አቢያተ ክርስቲያናት አዲስ ምርጫ ተደርጎ በቃለ ዓዋዲው መሠረት የሚተዳደር አንድ ቤተክርስቲያን ይሆናል ስሙም ደብረ ብርሃን ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ይባላል ነገር ግን የኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን የቦርድ አባላት ከቦርድ ወደ ሰበካ ጉባኤ ካልመጡ ይህን አሳብ ካልተቀበሉ እመኑኝ ቦታው የእናንተ ነው ብለው በመሐላ ጭምር ቃል ገብተውን ሪሞዴሊንጉ እንዲቀጥል ሆኗል።

ይሁን እንጂ ብጹእ አቡነ ናትናኤል ቃለ መሐላቸውን በማፍረስ የኪዳነ ምህረት ወይንም የማርያም ቤተክርስቲያን በቦርድ እየተዳደረ እያለ ከእኛ ነጥቆ የወሰደውን ቦታ በበላይነት እርሱ እየተቆጣጠረ እኛ ድምጽ መስጠትና መወስነ በማንችልበት መልኩ ሶስት ተወካይ ብቻ እንዲኖር በማድረግ ተገቢ የሆነ የኃላፊነትና የውክልና ቦታ ሳይሰጠን በእንግሊዘኛ በተጻፈ ደብዳቤ ሕጋዊ በሆነ መልኩ ከሃገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት ሊላክልን ሲገባው ከአንድ የኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን የቦርድ አባል በቴክስት የብጹእ አቡነ ናትናኤል ቲተርና ፊርማ ያለበት ደብዳቤ ደርሶናል።

በእኛ በኩል በአንድነት ለማገልገል የሚያስችል አማራጭ ሐሳብ አቅርበን ባለበት ወቅት ላቀረብረው አማራጭ ሐሳብ መልስ ባልተሰጠበት ሁኔታና ጉዳዩ ገና መቋጫ ባላገኘበት መልኩ ይህ ጽሑፍ መጻፉ ያሳዘንነ መሆኑን እንገልጻለን።

አንደኛ ብጹእ አቡነ ናትናኤል በቅዱስ ሲኖዶስ ምላተ ጉባኤ ከሃገረ ስብከቱ ከተነሡ በኋላ እኛው ትኬት ቆርጠን ለአማኑኤል ክብረ በዓል መጥተው በዓሉን አርብና ቅዳሜ ከእኛ ጋር አክብረው ስለተፈጠረው ነገር ሁሉ ይቅርታ ሲጠይቁን ቆይተው በማግስቱ እሁድ ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን ሄደው ይህን እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው የሆነ ውሳኔ መወሰናቸውና በአስቸኳይ ተጣድፈው በፊርማቸው የተረጋገጠ ደብዳቤ መጻፋቸው እጅግ አሳዝኖናል።

ይሁን እንጂ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ “እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን” ሮሜ ፰:፳፰

እኛም ይህ ለበጎ ነው ብለን ከበዚያን ጊዜ አንስቶ የራሳችንን ቤተክርስቲያን ለመሥራትም ሆነ ለመግዛት አቅደን በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን ይህን እቅዳችንን እውን ለማድረግ በምናደርገ ጥረት ሁሉ በመላው ዓለም የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ካህናትና ምዕመናን በሙሉ በጸሎት እንዲያስቡን በሚያስፈልገው ሁሉ ትብብርና ድጋፍ እንዲያደርጉልን በእግዚአብሔር ስም በአክብሮት እንጠይቃለን።